## የበርሊን ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን

በበርሊን ብራንደንቡርግ የቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ከመቋቋሙ በፊት በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ ለ፲፪ ዓመታት ያህል አልፎ አልፎ መንፈሳዊ አገልገሎት ሲሰጡና ሌሎችንም ካህናት ሲያስተባብሩ መኖራቸው ይታወቃል። በተለይም የበርሊን ግንብ ፈርሶ በምሥራቅ አውሮፓ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ከገቡ በኋላ የምእመናኑ ቁጥር እየጨመረ መሄዱ አልቀረም። በዚህም ጊዜ በቅድስት ማርያምና በቅዱስ ገብርኤል ስም የጽዋ ማኅበራት ተቋቁመው ብዙዎች ምእመናን መሰባሰብ ከጀመሩ በኋላ፤ የቤተ ክርስቲያኑ መመሥረት አስፈላጊ መሆኑን ካህናቱና ምእመናኑ አምነውበት የብዙ ጊዜ ውይይት ተካሂዷል። ብዙ ጊዜ ውጣ ውረድ እንደነበረበትም ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ የነበሩት ሁሉ በየጊዜው የሚያስታውሱት ትዝታ ነው። በተለይም እንጻሁኑ የትራንስፖርት ምቾት ባልነበረበት ጊዜ ከምዕራብ ጀርመን ተጉዞ በበርሊን ከተማ መንፈሳዊ አገልግሎት ማበርከት ቀላል እንዳልሆነ መገንዝብ ይቻላል። ታዲያ ብዙ መሥዋዕት ተከፍሎበታል ማለት ነው። ምንም እንኳን መንፈሳዊ አገልግሎት ማበርከቱ ዓላማቸው ቢሆንም፤ ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ ለበርሊን ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ያላሠለሰ ጥረት አድርገዋል። የእርሳቸውና የምእመናኑ ትብብር ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከረ በመሄዱ፤ ለ፫ ዓመታትም ያህል የበርሊን ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ድርጅት የደመወዝ ድጎማ በማድረጉ፤ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ቁርሎስ ቤተ ክርስቲያኑ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫/04.02.2001/ ዓ. ም ተባርኮ ታቦተ አማኑኤል እንዲገባ ተደርጓል። ታቦተ ሕጉ ገብቶ መንፈሳዊ አገልግሎት በቋሚነት መሰጠት ከጀመረ እነሆ ሁለት ዓመት ሁኖታል።

በዚህም ጊዜ ውስጥ ምእመናን በቃለ እግዚአብሔር እንዲጸኑ፤ ቅዳሴ እንዲያስቀድሱ፤ ሕፃናትም ጥምቀተ ክርስትና እንዲያገኙ ከመደረጉም በላይ ከሀገራችው የራቁትም በመንፈስ እንዲቀርቡ ለማድረግ ተሞክሯል።

ይህንን መንፈሳዊ አገልግሎት ለማሳደግ ቀደም ብሎ ተቋቁሞ የነበረው የሰበካ ጉባኤ መንፈሳዊ አስተዳደር በአባላት እንዲጠናከር ተደርጓል። በአዲስ መልክ የተጠናከረው የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር የሚጠበቅበትን መንፈሳዊ ተግባር ለመፈጸም ያመቸው ዘንድ ሥራዎቹን በአጭር፤ በመካከለኛና በረጅም ጊዜያት ከፍሎ፤ ይህንኑ ለማኅበረ ምእመናኑ በማስረዳት፤ ምእመናኑም የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እንዲያበረክቱ አሳስቧል። ማሳሰቢያውንም በጽሑፍ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል። በማሳሰቢያው ከተካተቱት ነጥቦች ጥቂቶቹ፤

፩/ ቤተ ክርስቲያኑን በሐሳብ እንዲረዱ፤

፪/ በሰበካ ጉባኤ አባልነት ያልተመዘገቡ ከሆነ እንዲመዘገቡና ክፍያ እንዲጀምሩ፤ ተመዝግበው

ከሆነም ለአሠራር ያመች ዘንድ ክፍያውን በባንክ ቤት እንዲያደርጉ።

፫/ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያልመጡትን ምእመናን እንዲመጡ መንፈሳዊ ግብዣ እንዲያደርጉ የሚሉ ይገኙባቸዋል።



በአሁኑ ጊዜ ምእመናኑ የሰበካ ጉባኤውን ጥሪ ተቀብለው አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ በማድረግ ላይ ናቸው። ከዚህ ላይ በአርአያነቱ ሳይ ጠቀስ የማያልፈው ምእመናኑ በራሳቸው አነሳሽነት ራሳቸውን በተወሰነ ቁጥር በማሰባሰብና ተጠሪ በመምረጥ፣ በተጠሪዎቻቸው አማካይነት የሚፈለግባቸውን የአሥራት ክፍያ ለመክፈል የሚያደርጉት ጥረት፣ በዓላት በሚከበሩበት ወቅት የሚቀርቡትን የምግብና የመጠጥ ዝግጅቶች ለማዘጋጀት የሚያደርጉት ትብብር፣ እንዲሁም በየሳምንቱ እሑድ የሚያዘጋጁት ጸበል ጸዲቅ ነው።

በቤተ ክርስቲያኑ ቁጥራቸው ፺ የሚሆኑ ምእመናን በአባልነት ቢመዘገቡም የሚጠበቅባቸውን የአሥራት ክፍያ በመክፈል ላይ ያሉ ግን ፵ የሚያህሉ ብቻ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ፲፪ቱ ክፍያቸውን የሚፈጽሙት በባንክ በኩል ነው። ለከፋዮች ቁጥር ማነስ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋነኝነት ከሚጠቀሱት አንዱ የምእመናኑ ከበርሊን ወደሌላ ቦታ መዛወር ነው።

ሌላው ሰበካ ጉባኤው ከፍተኛ ቦታ ሰጥቶ በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ያደረገበት ጉዳይ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ የሆኑትን ሕፃናት የማስተማሩን ሥራ ነው። በዚህም ጥረቱ ቀጥሎ ከጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ. ም. ጀምሮ ቁጥራቸው ከ፲ እስከ ፲፭ የሚሆኑ ሕፃናትን በማስተማር ላይ ይገኛል። ይህ ጥረት ተጠናክሮ ከቀጠለ ቁጥራቸው ከዚህ የበዛ ልጆችን ለማግኘት ይቻላል የሚል ተስፋ አለ።

የቤተ ክርስቲያኑ ሰንበት ት/ቤት ክፍል በአባልነቱ የጊዜ እጥረት ምክንያት የፈለገውን ያህል ሊሠራ ባይችልም፣ ቤተ ክርስቲያኑ በሚያከብራቸው ዓመታዊ በዓላትና ዓበይት በዓላት ላይ ለምእመናኑ ትምህርት ሰጭ የሆኑ መንፈሳዊ ድራማዎችን፣ መዝሙራትንና ልዩ ልዩ ሥነ ጽሑፎችን ያቀርባል። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኗ በምትጋበዝበት ጊዜ፣ በልዩ ልዩ ቦታዎች በመገኘትና መዝሙር በማቅረብ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ለዚህም አገልግሎቱ ይረዳው ዘንድ የተለያዩ ንዑሳን ክፍላትን በማቋቋም አባላቱን እንደዝንባሌያቸውና እንደፍላጎታቸው በእነዚህ ክፍላት ውስጥ በመመደብ እንዲሳተፉ እያደረገ ነው። በተጨማሪም አባላቱ በአሥራት ክፍያው ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው።

በቅርቡም ሰበካ ጉባኤው በሀገራችን በደረሰው ድርቅ ምክንያት በረሀብ ለተጎዱ ወገኖቻችን በጀርመን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀረበው የእርዳታ ጥሪ መሠረት ገቢው በዚህ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖቻችን የሚውል ዝግጅት አድርጓል። በዕለቱም ብዙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንዲሁም ጀርመናውያን ተገኝተው እርዳታ ከማድረጋቸውም በላይ በቀረቡት ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመጠኑ ለማስረዳት ተችሏል። በተለይም ጥንታዊ ስለሆነው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከባላሙያ ጋር ቃለ ምልልስ የተደረገ በመሆኑና ጥንታውያን ስለሆኑት የቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በሥዕል የተደገፈ ማብራሪያ በመስጠቱ፣ በዕለቱ ለተገኙ እንግዶች ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታውያን ቅርሶች የተወሰኑትን እንዲያውቁ ረድቷል።

እግዚአብሔር አምላክ ሥራችንን ይባርክ!

አባ ብርሃነ መስቀል ተድላ መንግሥቱ
የበርሊን ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ